# ክትባት ኤችፒቪ
## ከ ካንሰር ይከላከላል

PublicHealth
WELLINGTON-DUFFERIN-GUELPH
*Stay Well.*

ክትባት ኤችፒቪ -9 ለሁሉ ተማሪ፡ ከሁሉ ጾታ እና ከ12 አስከ 13 ዕድሜ ላሉ ይሰጣል። በመጀመርያዎች ዕድሜ፡ ከተጋላጭነት በፊት እና የበሽታ መከላከል ኣቅም ሃያል በሚሆንበት ግዜ ከተሰጠ የበለተ ውጤታማ ይሆናል። ይሄ ክትባት ለሁሉ ተማሪ እስከ 12ኛ ክፍል በነጻ ይሰጣል።

## የዚ ክትባት ስራ ምንድነው?

ኣብዛኞቹ ሰዎች በሂወት ዘመናቸው ከ ሁማን ፓፒሎማ ቫይረስ ንክኪ ይኖራቸዋል። ክትባት ኤችፒቪ ከ 9 የተለመዱ ከፍተኛ ኣደጋ ሊያስከትሉ ከሚችሉ የ ኤችፒቪ ኣይነቶች ይከላከላል።

- የጭንቅላት እና የኣንገት ካንሰር
- የማህጸን በር ካንሰር እና የሴት ብልት ካንሰር
- የፊንጢጣ ካንሰር
- የወንድ ብልት ካንሰር
- የብልት ኪንታሮት

## 3 ክትባት ኤችፒቪ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚወሰድበት ምክንያቶች

### ይሰራል!

ኣንድ ሙሉ በተከታታይ የተወሰደ ክትባት ኤችፒቪ፡ ታች ከተገለጹ በሽታዎች ይከላከላል፡

- ከ 90%% በላይ የ ማህጸን በር ካንሰር እና የ ብልት ኪንታሮት
- ኣብዛኞቹ የ ፊንጢጣ፡ የሴት ብልት፡ የሴት ብልት የ ውጭ ክፍል፡ የወንድ ብልት፡ የኣፍ እና የጎሮሮ ካንሰሮች

### ኣስተማማኝ ነው!

በ ዓለም ዙርያ ያሉት በሚልዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ኤችፒቪ ክትባትን በ ኣስተማማኝ መንገድ ወስደዉታል። ጎንዮች ጉዳቶች ኣብዛኛው ጊዜ ቀለል ያሉ ናቸው፡ ኣስተማማኝነቱ ደሞ በተከታታይ ክትትል ይደረግለታል።

### ቀላል ነው!

ነርስ ክትባት ኤችፒቪ ለመስጠት ወደ ልጆቻቹ ትምህርት ቤት ይመጣሉ- ቀጠሮ ማስያዝ ይሁን ዕረፍት መውሰድ ኣያስፈልግም። የፍቃድ ቅጹን ብቻ በቀላሉ ሙሉት።

## የ ኤችፒቪ ክትባት ጥቅሞች

1. **ከ ካንሰር ይከላከላል**
2. **ከ ተጋላጭነት በፊት ከተሰጠ የበለጠ ይሰራል**
3. **እስከ መጨረሻ 12ኛ ክፍል በነጻ ነው**
4. **ከ ብልት ኪንታሮት ይከላከላል**
5. **ለረዥም ጊዜ ይከላከላል**
6. **ኣስተማማኝ እና ጥሩ ጥናት የተደረገለት ነው**



### የፍቃድ ቅጹን ለመሙላት ዝግጁ ናቹ?

**ኪው ኣር ኮዱን ቅረጹት ወይ እዚ ውስጥ ይግቡ**
**wdgpublichealth.ca/Gr7Consent**

### ለሚኖራቹ ጥያቄዎች

**1-800-265-7293 ተጨማሪ ቁጥር 7006**
**wdgpublichealth.ca/HPVfacts**

**ይሄን ቅረጹት**

# የጉበት በሽታ ‘ቢ’ ክትባት

## ከ ጉበት ኢንፈክሽን ይከላከላል

PublicHealth
WELLINGTON-DUFFERIN-GUELPH
*Stay Well.*

‘የጉበት በሽታ ‘ቢ’ ክትባት ለሁሉ ተማሪ፡ ከሁሉ ጾታ እና ከ12 እስከ 13 ዕድሜ ላሉ ይሰጣል። በመጀመርያዎች ዕድሜ፡ ከተጋላጭነት በፊት እና የበሽታ መከላከል ኣቅም ሃያል በሚሆንበት ግዜ ከተሰጠ የበለተ ውጤታማ ይሆናል። ይሄ ክትባት ለሁሉ ተማሪ እስከ 12ኛ ክፍል ላሉት በነጻ ይሰጣል።

## የዚ ክትባት ስራ ምንድነው?

የጉበት በሽታ ‘ቢ’ ክትባት ከ ጉበት በሽታ ‘ቢ’ ቫይረስ ይከላከላል። ይሄ ቫይረስ የጉበት ጉዳት፡ የጉበት ካንሰር እንዲሁም ሞት ልያስከትል ይችላል። ‘ቢ’ ኣይነት የጉበት በሽታ በዋነኝነት የ ጉበት ካንሰር በ ካናዳ ያስከትላል።

## 3 ትምህርት ቤት ውስጥ የጉበት በሽታ ‘ቢ’ ክትባት የሚወሰድበት ምክንያቶች

### ይሰራል!

በጉበት በሽታ ‘ቢ’ ከተያዙት 10 ሰዎች መሃል ኣንዱ በሂወት ዘመኑ ሙሉ በሽታዉን ይሸከመዋል። ክትባቱን መውሰድ፡ በጊዜ ሂደት ሊመጡ የሚችሉ የ ጤና ኣደጋዎችን ለማስወገድ የበለጠ መንገድ ነው። የጉበት በሽታ ‘ቢ’ ክትባት በጣም ውጤታማ ነው። በትክክለኛው መጠን ከተሰጠ 98% ሰዎችን ይከላከልላቸዋል።

### ኣስተማማኝ ነው!

የጉበት በሽታ ‘ቢ’ ክትባት በጥንቃቄ መርመራ የተደረገለት ሆኖ ኣስተማማኝነቱም በተከታታይ ክትትል ተደርጎለታል። የሚያስከትለው የሰውነት ቁጣ ኣብዛኛው ጊዜ ቀለል ያለ ነው። ልጆቻቹ በ ጉበት በሽታ ‘ቢ’ ከሚያዙ ክትባቱን ቢወስዱ ኣስተማማኝ ይሆናል።

### ቀላል ነው!

ነርስ የጉበት በሽታ ‘ቢ’ ክትባት ለመስጠት ወደ ልጆቻቹ ትምህርት ቤት ይመጣሉ- ቀጠሮ ማስያዝ ይሁን ዕረፍት መውሰድ ኣያስፈልግም። በቀላሉ የ ፍቃድ ቅጹን ብቻ ይሙሉት።

## የጉበት በሽታ ‘ቢ’ ክትባት ጥቅሞች



1. ከጉበት በሽታዎች እና ከጉበት ካንሰር ይከላከላል
2. ከተጋላጭነት በፊት ከተሰጠ የበለጠ ይሰራል
3. እስከ መጨረሻ 12ኛ ክፍል በነጻ ነው
4. ለረዥም ግዜ ይከላከላል
5. ኣስተማማኝ እና ጥሩ ጥናት የተደረገለት ነው

### የፍቃድ ቅጹን ለመሙላት ዝግጁ ናቹ?

**ኪው ኣር ኮዱን ቅረጹት ወይ እዚ ውስጥ ይግቡ**
wdgpublichealth.ca/Gr7Consent

### ለሚኖራቹ ጥያቄዎች

**1-800-265-7293 ተጨማሪ ቁጥር 7006**
wdgpublichealth.ca/HepBfacts

ይሄን ቅረጹት

# ክትባት መኒንጎኮካል ኮንጁጌት-ኤሲዋይዳብሊው

## ከ መኒንጎኮካል በሽታዎች ይከላከላል

**ይህ ክትባት ለሁሉ ተማሪ፡ ከሁሉ ጾታ እና ከ12 አስከ 13 ዕድሜ ላሉ ይሰጣል። በመጀመርያዎች ዕድሜ፡ ከተጋላጭነት በፊት እና የበሽታ መከላከል ኣቅም ሃያል በሚሆንበት ግዜ ከተሰጠ የበለተ ውጤታማ ይሆናል። ይሄ ክትባት ለሁሉ ተማሪ እስከ 12ኛ ክፍል በነጻ ይሰጣል።**

## የዚ ክትባት ስራ ምንድነው?

ክትባት መኒንጎኮካል ኮንጁጌት ልጆትን ከ መኒንጎኮካል በሽታዎች ይከላከላል፡ ይህ ለሂወት በሚያሰጋ የ ባክተርያ ኢንፈክሽን የሚመጣ ሆኖ፡ መስማት መሳን፡ እንፍርፍሪት፡ የኣንጎል ጉዳት፡ የ እግሮች መጉደል እንዲሁም ሞት ልያስከትል ይችላል።

## 3 ትምህርት ቤት ውስጥ ይሄ ክትባት የሚወሰድበት ምክንያቶች

### ይሰራል!

ክትባት መኒንጎኮካል ኮንጁጌት- ኤሲዋይዳብሊው መኒንጎኮካል በሽታዎች ለመከላከል ከ 80-85% ውጤታማ ነው። በሽታው በቀላሉ በ ሳል፡ ማስነጠስ፡ ወይም ኣብሮ በመብላት እና መጠጣት ይተላለፋል። በዚ በሽታ ከታመሙት 100 ሰዎች ኣንዱ በሂወት ኣይቀጥልም።

### ኣስተማማኝ ነው!

ይህ ክትባት በጥንቃቄ መርመራ የተደረገለት እና ኣስተማማኝነቱም በተከታታይ ክትትል ተደርጎለታል። የሚያስከትለው የሰውነት ቁጣ ቀለል ያለ ነው። ልጆቻቹ በ መኒንጎኮካል በሽታ ከሚያዙ ክትባቱን ቢወስዱ ኣስተማማኝ ይሆናል።

### ቀላል ነው!

ነርስ ክትባት መኒንጎኮካል ኮንጁጌት-ኤሲዋይዳብሊው ለመስጠት ወደ ልጆት ትምህርት ቤት ይመጣሉ—ቀጠሮ ማስያዝ ይሁን ዕረፍት መውሰድ ኣያስፈልግም። የ ፍቃድ ቅጹን ብቻ በቀላሉ ይሙሉት።

## የ ክትባት መኒንጎኮካል ጥቅሞች

1. **ከባድ ከሆነ ኢንፈክሽን ይከላከላል**
2. **ከተጋላጭነት በፊት ከተሰጠ የበለጠ ይሰራል**
3. **እስከ መጨረሻ 12ኛ ክፍል በነጻ ነው**
4. **ለረዥም ጊዜ ይከላከላል**
5. **ኣስተማማኝ እና ጥሩ ጥናት የተደረገላት ነው**



## የፍቃድ ቅጹን ለመሙላት ዝግጁ ናቹ?

**ኪው ኣር ኮዱን ቅረጹት ወይ በዚ ይግቡ**

**wdgpublichealth.ca/Gr7Consent**

## ለሚኖራቹ ጥያቄዎች

**1-800-265-7293 ተጨማሪ ቁጥር 7006**

**wdgpublichealth.ca/MenCfacts**

**ይሄን ቅረጹት**

PublicHealth
WELLINGTON-DUFFERIN-GUELPH
Stay Well.